# ስለ "እውነት" እውነቱን ልንገራችሁ!

ከተስፋዬ ሮበሌ

ወርኀ መስከረም 1999 ዓ.ም

## *መግቢያ*

***"እውነት" ምንድን ነው? "እውነትን" እውነት የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው?***

*"እውነት" የሚባል ነገር አለ? በርግጥ "እውነት" የሚባል ነገር ካለ እውነት ምንድን ነው? እውነት ከሰው ሰው፣ ከቦታ ቦታ፣ ከሁኔታ ሁኔታ የሚቀያየር አንጻራዊ ምልከታ ነው ወይስ በአንዳችም ቅድመ ሁኔታ የማይገደብ ነባራዊ መሠረት*[1]::

*"እውነትን" አስመልክቶ የሚካሄዱ ውይይቶች በሁለት መሠረተ ነጥቦች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው:: ይኸውም "እውነት" ምንድን ነው? "እውነትን" እውነት የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው (ካለ ማለት ነው)?:: ይህ በሺህዎች ለሚቈጠሩ ዓመታት እጅግ ሰፊ ውዝግብ የተካሄደበት ርእሰ ጕዳይ ነው—በተለይ ሥነ ዕውቀት በሚባለው የፍልስፍና ጥናት ዘርፍ ውስጥ::*

*ወርኀ ጥር 2000 ዓ.ም ላይ፣ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛው ፕሮግራም በሁለት ተከታታይ ፕሮግራሞች፣ "እውነት ምንድን ነው? ሰዎች ለምን ይዋሻሉ?" በሚል ሦስት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንን በርእሰ ጕዳዩ ላይ አወያይቶ ነበር:: ተናጋሪዎቹ የሥነ ልቡና የትምህርት ዘርፍ፣ የፍልስፍና የትምህርት ዘርፍ እንዲሁም የማኅበረሰብ ጥናት የትምህርት ዘርፍ ምሁራን ሲሆኑ፣ በተማሩበት የትምህርት ዘርፍ የዶክትሬት ዲግሪ ያገኙ ናቸው::*

*እንደነዚህ ምሁራን አቋም፣ እውነት በግለሰቦች ወይም በማኅበረሰብ ፍላጎት የምትወሰን አንጻራዊ ምልከታ ነች እንጂ ጊዜን፣ ሁኔታንና ቦታን የምትሻገር ነባራዊ መሠረት ያለመሆኗን ለመሞገት ሞክረዋል:: አንድ ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ፣ "እውነት" ወይም "ሐሰት" የሚላቸው ጕዳዮች ከሌላው ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ፍጹም የተለዩ ሆነው መገኘታቸው እውነት አንጻራዊ መሆኗን የሚያሳይ ነው የሚለው ነጥብ የሙግታቸው አካል ነበር::*

*እነዚህ ምሁራን "እውነት" ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ ከተማሩበት የትምህርት ዘርፍ አንጻር ለማብራራት ቢሞክሩም፣ ሁሉም ተናጋሪ ስለ"እውነት" ያቀረበው ግላዌም ሆነ ትንታኔ እስከ 1914 ዓ.ም ተቀባይነት የነበረውንና አሁንም በስፋት የሚሠራበትን* ***የዝምደታዊ/የጕድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ*** (Correspondence Theory of Truth) *መሠረት ያደረገ ሳይሆን፣ ይህን ንድፈ ሐሳብ ከሚጣረሱ ተጻራሪ የእውነት ንድፈ ሐሳቦች*[2] *በቀጥታ*

---

[1] *ይህ ጽሑፍ ፕላስ አርት ሚኒስትሪ ወርኀ የካቲት 2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ አዘጋጅቶት በነበረው ዐውደ ጥናት ላይ የቀረበ ጽሑፍ ነው:: በርእሰ ጕዳዩ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የመጽሐፉ ጸሓፊ፣ የሥነ ምግባር መርሖ (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም) በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ እንዲሁም በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ በዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር ላይ ያሉትን መጻሕፍት ይመለከቷል::*

[2] *ይኸውም **ቅንብራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ** (coherence theories of truth) እንዲሁም **ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ** (pragmatist theories of truth) ናቸው::*

የተቀዳ ነው። እነዚህ ንድፈ ሐሳቦች ደግሞ የግብረገባዊ አንጻራዊነትም ሆነ ***የግንዛቤያዊ አንጻራዊነት*** (Cognitive Relativism) መሠረቶች ናቸው። አስገራሚው ጉዳይ እስከ ዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በየትኛውም የትምህርት ዘርፍ ውስጥ ስለ"እውነት" የሚቀርበው ግላዊም ሆነ ትንታኔ፣ "እውነት" ነባራዊ እንደ ሆነች የሚያሳይ ነበር (*የዝምደታዊ/የጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ መሠረት ያደረገ* ነበር)። በሃያና በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግን እውነት ነባራዊ ነች የሚለው ጉዳይ ጊዜ ያለፈበት ምናልባትም በቀለም ትምህርት ገፍቶ ያለመሄድ ምልክት፣ አንጻራዊ ነች የሚለው ግን የቀለም ቀንድነት ትእምርት ተደርጎ መወሰድ ጀምሮአል ቢባል እብለት ግነት የለበትም (ዛሬም እውነት ነባራዊ ነች የሚሉ እጅግ የተከበሩና ስመ ጥር  ኀላያን መኖራቸው ባያከራክርም)።

**እ**ንዲያውም የቀደመው ዓለም በማይቀበለውና ትክክል ነው ብሎ በማያምንበት መልኩ "እውነት" የመተንተኗ ጉዳይ፣ ይህን ታሪካዊ ወቅት ድኅረ ዘመናዊ ዓለም (Postmodern Age) በመባል እንዲታወቅ (እንዲሰየም) ምክንያት ሆኖአል።

**አ**ንድን የታሪክ ዘመን ከሌሎች የታሪክ ዘመናት ጋር በተነጻጸረ መልኩ ለዘመኑ ስያሜ ማውጣት የተለመደ አሠራር ነው። ለምሳሌ ከየትኛውም የታሪክ ጊዜ አንጻር ሲታይ ሥልጣኔ አንዳችም ዕድገት ያላሳየበትንና ድንቊርና የነገሠበትን፣ ከ476 ዓ.ም ጀምሮ  እስከ 1000 ዓ.ም ያለው የታሪክ ጊዜ **የጨለማው ዘመን** (Dark Ages) በመባል እንዲታወቅ ምክንያት ሆኖአል። ከ1350 ዓ.ም እስከ 1600 ዓ.ም ያለው ጊዜ ደግሞ አውሮፖውያን በሥልጣኔ ያደጉበት፣ በማተሚያ መሣሪያ ምጽአት አማካይነት ዕውቀት የተስፋፋበት፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ፣ ሥነ ጥበብ፣ ቅኔ፣ ሥነ ሕንፃ ታላቅ ደረጃ የደረሱበት እንዲሁም የሥልጣኔ ጅማሪ ተደርጎ የሚወሰድ ውቅት ስለሆነ ይህ ታሪካዊ ወቅት **የዕውቀት ዳግም ልደት** (Renaissance) በሚል ስያሜ እንዲታወቅ የግድ ብሎአል።

**አ**ብራኄ ኀሊና ዘመን** (Age of Enlightenment) የሚባለው በዐሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ በአውሮፓ የተነሣውን ፍልስፍና ለማመልከት ወይም ከዐሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ያለውን የምክንዩን የበላይነት የሚያጸናና ሁሉ ነገር በአእምሮ ጥያቄ ውስጥ መውደቅ አለበት ብሎ የሚሟገት ንቅናቄ ነው። ከዚህ ዐይነተኛ ባሕርይው የተነሣ ይህ ዘመን፣ **ዘመነ አመክንዮ** (Age of Reason) ተብሎ ተጠርቶአል። አብራኄ ኀሊና ዘመን ሥነ ውበት፣ ሥነ ምግባር እንዲሁም ሥነ አመክንዮ በአጠቃላይ እውነትና ውሸት፣ እኩይና ሠናይ የሚወሰነው በምክንዩ ነው የሚል ምክንዮ በሁሉ ነገር ላይ ያለውን ሥልጣናዊነት የተነጸባረቀበት ዘመን ነው። ከዚህ የተነሣም አብራኄ ኀሊና ዘመን የነበሩት ኀላይያን ራሳቸው ዓለምን ወደ ዕድገትና ለውጥ የሚመሯት የዕውቀት ሐዋርያት አድርገው ራሳቸውን የመለከታሉ። በአጠቃላይ ዘመነ አመክንዮ በጨለማው ዘመን ነግሦ የነበረውን ኢምክንዮአዊነት፣ ጥንቈላ፣ ጭቈና፣ ክፉኛ የሚቃወም ንቅናቄ ነው። በአሜሪካና በፈረንሳይ የታየውን አብዮት፣ በደቡብ አሜሪካ የታየውን የነጻነት እንቅስቃሴ፣ ኋላም የለዘብተኛነትና የሳሻሊዝም ጥንስሱ አብራኄ ኀሊና ዘመን የታየው የአፍቃሬ አመክንዮ ንቅናቄ ነው።

**ዘ**መነ ተሐድሶ** (Protestant Reformation) በመባል የሚጠራው በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በምዕራብ አውሮፓ በመትገኘው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመርሐያነ ተሐድሶዎች በተለይም በወርኀ ጥቅምት 1517 ዓ.ም በጀርመን አገር በማርቲን ሉተር አማካይነት የተነሣውን የእምነት ተሐድሶ ንቅናቄ የሚያመለክት ነው። ከዘመነ ተሐድሶ ንቅናቄ አማካይነት የተወለዱት አራቱ ዐበይት መንፈሳዊ ትውፊቶች ማለትም የሉትራውያን ትውፊት፣ የተሐድሶ (የካልቪኒስቶች ወይም የፕርስቢቴሪያን) ትውፊት፣ የዳግም መጥምቃውያን ትውፊት እንዲሁም የአንግሊካን (የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን) ትውፊት ናቸው። በዚህ ዘመን ውስጥ በርካታ የነገረ

መለኮት ትምህርት ቤቶች የተከፈቱ ሲሆን፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮና መዋቅራዊ ተዋረድ የሚተነትኑ ተቋማት ተጀመሩ::

**ዘመናዊ** (Modernism) በመባል የሚታወቀው ዘመን፣ ከዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እንዲሁም በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ እስከ 1914 ዓ.ም ያለው ጊዜ ነው::

**ድኅረ ዘመናዊ** (Postmodernity) በመባል የሚታወቀው የታሪክ ወቅት ፈላስፎች፣ ማኅበራዊ ሳይንቲስቶች፣ የሥነ ሥዕል ሐያስያን ወቅታዊውን (ማለትም ከሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻና ከሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንሥቶ ያለውን ጊዜ) ባህል፣ ሥነ ሥዕል፣ ሥነ ምጣኔ እንዲሁም ማኅበራዊ ሁኔታ ለማመልከት ቃሉን ይጠቀሙበታል:: የዚህ ዘመን ዐይነተኛ ባሕርያት ተደርገው የሚወሰዱት ድንበር የለሹ የንግድና የባህል ሥርዐት፣ ከአምራችነት ይልቅ ተጠቃሚነት በሕዝቦች ዘንድ መሠልጠኑ፣ ዕውቀት እንደ ሸቀጥ መታየቱ፣ እንዲሁም እውነት ነበራዊ ሳትሆን ኅሊናዊ ነች የሚለው አመለካከት ነው::

"እውነት" ምንድን ነው? "እውነትን" እውነት የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው የሚለው ጉዳይ መሠረታዊ የመሆኑን ያህል ከመቼውም የታሪክ ጊዜ ይልቅ አወዛጋቢ የመሆኑ ጉዳይ ይህን ዐውደ ጥናት ልዩ ያደርገዋል:: ርእሰ ጉዳዩ ረቂቅ ቢሆንም፣ ነባቢያን ወንቀኡን የሆኑ የሰው ልጆች ሁሉ፣ በተለይም አፍቃሬ እውነት የሆንን ክርስቲያኖች በትምህርቱ አስቸጋሪነትና ውስብስብነት ሳንፈታ ጊዜ ሰጥተን ልንመረምረው ይገባል::

"እውነት" ምንድን ነው የሚለው ጥያቄ ለክርስትና ሃይማኖትም ሆነ መሠረተ እምነት ምሶሶና ማገር ነው:: ክርስትና እኔ "በዝምደታዊ/በጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ አምናለሁ" የሚል አንቀጸ ሃይማኖት ባይኖረውም፤ አስተምህሮው የተዋቀረው ይህን የእውነት ንድፈ ሐሳብ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ለመሆኑ አያከራክርም:: ክርስትና "እውነት" ከገሐዱ ዓለም ጋር (reality) አንድ የመሆን ጉዳይ ነው የሚል ሃይማኖት ነው::

# I. አንጻራዊነት ማለት ምን ማለት ነው?

"እውነት" ምንድን ነው? እንዲሁም አንጻራዊነት ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጉዳይ ከማየታችን በፊት:—

(1) **ነባራዊ እውነት** (Objective Truth) **ማለት ምን ማለት ነው?** (2) **ኅሊናዊ እውነት** (Subjective Truth) **ማለት ምን ማለት ነው?** (3) **ምክንዮአዊ እውነት** (Rational or Cognitive Truth) **ማለት ምን ማለት ነው? እንዲሁም** (4) **ግብረገባዊ እውነት** (Moral Truth) **ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጉዳይ እንመልከት:—**

በቅድሚያ ነባራዊ እውነትንና ኅሊናዊ እውነትን በንጽጽር እንይ:—

1. የጉመን ወጥ እወዳለሁ::
2. የጉመን ወጥ አንዳችም ቫይታሚን ባይኖረው ደስ ይለኛል::
3. የጉመን ወጥ ቫይታሚን የለውም::

የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ግለሰቡ በጐመን ወጥ ላይ ያለውን የራሱን አስተያየት/ጣዕምና እየተናገረ እንጂ፣ ስለ ጐመን ወጥ እየተናገረ አይደለም። አንድ ሰው ይህን ነገር በመናገሩ ንግግሩ እውነትም ሆነ ሐሰት አይደለም[3]። ይህ ኅሊናዊ እውነት ይባላል። አንድ ሰው "የጐመን ወጥ እወዳለሁ" ብሎ በመናገሩ "እንዴት የጐመን ወጥ ትወዳለህ?" ይህ "ስሕተት ነው" ወይም "ትክክል ነው" ማለት አንችልምና።

የጣዕምናን ጉዳይ ወደ ጐን ትተን ሁለተኛውን ዐረፍተ ነገር ስንመለከት ግን ጐመን ቫይታሚን አለው ወይም የለውም የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው በግለሰቡ "ደስታ" ወይም ፍላጎት ሳይሆን፣ ነባራዊ በሆነውና ጐመን በውስጡ በያዘው ወይም ባልያዘው ቫይታሚንነት ብቻ ነው። ጐመን ቫይታሚን አለው ወይም የለውም የሚለው ውዝግብ የሚፈታው በግለሰቦች በጐ ፍላጎት ወይም ጣዕምና ሳይሆን፣ ጐመን ይዞት በሚገኘው ወይም በማይገኘው የቫይታሚን ይዘት ነው። ተፈትሾ በሚገኘው ውጤት ቫይታሚን አለው ወይም የለውም የሚለው ጉዳይ ይወሰናል። ፍተሻውን የምናካሂደው ተመሳሳይ ስሜት ወይም ጣዕምና ለመጋራት ሳይሆን እውነታውን ለማወቅ ነው።

የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ኅሊናዊ እውነታን የሚያመለክት ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ጐመን በውስጡ የያዘውን ቫይታሚንነት ኅሊናዊ በሆነ መንገድ ለመበየን የተካሄደ ጥረት ስለሆነ ስሕተት ነው። ሦስተኛው ዐረፍተ ነገር ግን ነባራዊ የሆነውን ጉዳይ ነባራዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት የተደረገ ሙከራ ነው—ምንም እንኳ የዐረፍተ ነገሩ እውነት ፋይዳ (Truth Value) ስሕተት ቢሆንም።

4. ወላጆቻችንን ልናከብር ይገባናል።
5. ሞያሌ በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል የምትገኝ የድንበር ከተማ ነች።

እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች የተለያየ ባሕርይ አላቸው። የመጀመሪያው ስለ ግብረገብ የሚናገር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ስለ መልክዐ ምድር የሚያወራ ነው። ስለዚህ በቁጥር 4 ላይ የሚገኘው ዐረፍተ ነገር ግብረገባዊ ርእሰ ጉዳይን የሚመለከት ስለሆነ ግብረገባዊ እውነት በመባል ይጠራል። አምስተኛው ዐረፍተ ነገር ግን ከግብረገብ ርእሰ ጉዳይ ውጪ በመሆኑ ምክንያት ምክንዩአዊ ወይም ግንዛቤያዊ እውነት (Rational or Cognitive Truth) ይባላል[4]።

አሁን አንጻራዊ ወይም ነባራዊ የሚባሉትን ሐሳቦች መፍታት እንችላለን። ምክንዩአዊም ሆነ ግብረገባዊ እውነታዎች እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰቦች ብያኔ ይወሰናሉ የሚል አመለካከት አንጻራዊነት ይባላል። በሌላ አገላለጽ እውነት በቦታ፣ በጊዜና በሁኔታ የምትወሰን ነች የሚለው አመለካከት አንጻራዊነት የሚባል ሲሆን፣ እውነት በቦታ፣ በጊዜና በሁኔታ አይወሰናትም የሚለው አመለካከት ደግሞ ፍጹማዊነት ወይም ነባራዊነት ይባላል።

[3] በሥነ አመክንዮ ቋንቋ እውነት ወይም ሐሰት መሆን የማይችል ዐረፍተ ነገር "Proposition" አይባልም። አስተያየት፣ ጥያቄ፣ ምክር ወዘተ የእውነት ፋይዳቸው (Truth Value) እውነትም ሆነ ሐሰት ስለማይሆን በሥነ አመክንዮ "Proposition" አይባሉም።

[4] ክርስቲያኖች ለስሕተቶቻቸው ሁሉ በእግዚብሔር ፊት ንስሓ መግባት አያስፈልጋቸውም። "ሞያሌ የናይጄሪያ መናገሻ ከተማ ነች" የሚል አቋም የነበረው ክርስቲያን፣ ይህ ስሕተት እንደ ሆነ ቢረዳ አቋሙን ማስተካከል እንጂ ለስሕተቱ ንስሓ መግባት አያስፈልገውም። ክርስቲያኖች በእግዚብሔር ፊት ንስሓ የሚገቡት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ በስሕተትም ሆነ በድፍረት በተላለፉባቸው ግብረገባዊና ሃይማኖታዊ ትእዛዛት ላይ ብቻ ነው።

ግበረገባዊና ምክንዩአዊ እውነታዎች እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰቦች ፍላጎት ወይም ጣዕምና ይወሰናሉ የሚለው አመለካከት ግብረገባዊ አንጻራዊነት በመባል ሲታወቅ፣ ምክንዩአዊ እውነታዎች አንጻራዊ ናቸው የሚለው አመለካከት ደግሞ ምክንዩአዊ አንጻራዊነት ይባላል፡፡

ጥንታውያን ሰዎች መሬት እንደ ሰፌድ ጠፍጣፋ ነች ቢሉና ዘመነኞቹ ይህን ቢቀወሙ የአመለካከት ለውጥ እንጂ የእውነት ለውጥ አልተካሄደም፡፡ በሬት እንደ ሰፌድ ጠፍጣፋ ከመሆን እንደ እንቀኣላል ድብልብል ወደ መሆን ተቀይራለች ማለት አይደለም፡፡ "በዐጸደ ሥጋ ለመኖር በየቀኑ የኢንሱሊን መርፌን መውሰድ ያስፈልጋል" የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ እውነት የሚሆነው ለሱካር ሕመምተኞች ብቻ እንጂ ለሁሉም ሰው አይደለም፡፡ "ወብቆኛል" የሚለው አነጋገር ለአንዱ ሰው እውነት ሲሆን ለሌላው ሰው ግን እውነት ላይሆን ይችላል (በዚሁ ወቅት ሌላው ሰው ቅዝቃዜ ተሰምቶት ሊሆን ይችላል)፡፡ እኔ ተስፋዬ ሮበሌ የካቲት 22 ቀን 2000 ዓ.ም፣ 3 ሰዓት ከ38 ደቂቃ ላይ ወብቆኝ ነበር የሚለው ዐረፍተ ነገር ለእኔ ብቻ ትክክል ሊሆን ይችላል፤ ነገረ ግን ለእኔ ትክክል ከሆነ ለሁሉም ሰው ትክክል ስላልሆነ ስሕተት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ንግግሩ ፍጹማዊ እውነት ነው፡፡ መምህሩ የክፍሉ ዋነኛ በር ከእኔ በስተ ግራ በኩል ነው የሚገኘው ቢል፣ ከተማሪዎቹ ደግሞ በስተቀኝ በኩል ነው፤ ስለዚህ እውነት እንደ ግለሰቡ አተያይ አንጻራዊ ነው ማለት ስሕተት ነው፡፡ ለመምህሩ በስተግራ መሆኑ እውነት የሆነውን ያህል ለተማሪዎቹ ደግሞ በስተቀኝ ነው፡፡ የመምህሩና የተማሪዎቹ አቀማመጥ መለያየት የበሩን አቅጣጫ አይቀይረውም፡፡ ነገር ግን የነገሩ እውነት ከተናጋሪው ወይም ከዐረፍተ ነገሩ አንጻር መዳኘት ይኖርበታል፡፡ 7+3=10 የሚለው የሒሳብ እውነታ በየትኛውም ዘመን ለሚኖርና በማንኛውም ቦታና ሁኔታ ለሚገኝ ሰው እውነት ነው፡፡ ይህ እውነት ለሒሳብ ምሁራን ብቻ ወይም የሒሳብ ትምህርት በሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ ብቻ እውነት አይደለም፡፡

እውነት ነባራዊ ነች የሚለው ንድፈ ሐሳብ መሠረታዊ ናቸው የሚባሉትን ሦስት የሥነ አመክንዮ ሕጎች ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ይኸውም:—

(1) ያውነት/መሀንነት ሕግ (Law of Identity)

P= ሁለት ተጋማሽ ቍጥር (even number) ነው፡፡

Q= ሣር አረንጓዴ ቀለም ያለው ተክል ነው፡፡

የያውነት/የመሀንነት ሕግ አንድ ነገር (ለምሳሌ ከ"P") ከራሱ ጋር አንድ ነው እንዲሁም ከሌላ ነገር ፈጽሞ ይለያል (ለምሳሌ ከ"Q")[5]፡፡

(2) ቅራኔ አልባ ሕግ (Law of NonContradiction)

"P" በአንድ ጊዜና በአንድ ትርጕሙ እውነትና ሐሰት መሆን አይችልም[6]፡፡

(3) ማዕከለ ውጋጅነት/አግልሎት ሕግ (Law of Excluded Middle)

"P" እውነት አልያም ሐሰት ብቻ ነው የሚሆነው[7] እንጂ በአንድ ጊዜና በአንድ ትርጕሙ እውነትና ሐሰት መሆን አይችልም፡፡

---

[5] P is identical to itself and different from other things.

[6] P cannot be both true and false in the same sense at the same time.

[7] P is either true or false or, either P is true or its negation, not -P is true.

እነዚህ የሥነ አመክንዮ መሠረታዊ ሕግጋት፣ አንድ ግለሰብ የርእሰ ጉዳዩን (ለምሳሌ የ"P"ን) እውነትነትና ሐሰትነት ማወቅ ወይም ማረጋገጥ ቢችልም ሆነ ባይችል፣ ርእሰ ጉዳዩን (ለምሳሌ "P"ን) እውነት አልያም ሐሰት ከመሆን አይታደገውም የሚለውን መርሐ መሠረት ያደረገ ነው:: ለምሳሌ ቀለም አይለዩ (colorblind) የሆነ ሰው የ"Q" እውነትነት ወይም ሐሰትነት ላይለይ ይችላል፤ ነገር ግን "Q"ን እውነት አልያም ሐሰት ከመሆን አያስጥለውም::

እነዚህ የሥነ አመክንዮ ሕግጋት የምንማረው ሐቅ:—

1. አንጻራዊነት እውነት አልያም ሐሰት እንጂ ሁለቱንም መሆን በፍጹም አይችልም:: አንጻራዊነት እውነት ከሆነ እውነት የለም እያለ እኔ ራሴ እውነት ነኝ ማለት ስለሚሆን እርስ በርሱ በተቃርኖ ውስጥ ይወድቃል:: ሐሰት ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ኀሊናዊ ብያኔ ስለሚሆን የግለሰቡን ምርጫ፣ ባህል፣ አመለካከት ወዘተ የሚወክል እንጂ ነባራዊ ስለሆነ እውነት የሚናገር አይሆንም:: ሰዎች ሁሉ ሊቀበሉት የሚገባ ጉዳይ ነው ልንል አንችልም::

2. ጥንታውያን ሰዎች መሬት እንደ ሰፌድ ጠፍጣፋ ነበረች የሚል እምነት ነበራቸው፤ በዚህ ዘመን የምንኖር ሰዎች ግን ይህ ስሕተት እንደ ሆነ እናውቃለን:: ጥንታውያን ሰዎች መሬት ጠፍጣፋ ነች የሚል መረዳት ነበራቸው የሚለው አነጋገር እውነት ነው (በሥነ ዕውቀት ደረጃ):: ነገር ግን በዚያን ዘመን መሬት እንደ ሰፌድ ጠፍጣፋ የነበረች ሲሆን፣ በዚህ ዘመን ደግሞ ከጠፍጣፋነት እንደ እንቁላል ሞላላ ወደ መሆን ተቀይራለች (በኑባሬ ደረጃ) ማለት አይደለም::

3. እውነት አንጻራዊ ነች የሚለው አመለካከት የእውነትን ቅድመ ሁኔታና የእውነትን መስፈርት የሚደባልቅ ነው:: የእውነት ቅድመ ሁኔታ (a truth condition) የምንለው እውነትን እውነት የሚያሰኘው መሠረታዊ ማንነት/ኑባሬ (ontology) ነው:: ለምሳሌ አበበ በመካነ ኢየሱስ ሴሚነርዮም ነገረ መለኮት ይማራል የሚለው ዐረፍተ ነገር እውነት የሚሆነው አበበ የተባለው ሰው በተባለበት ቦታ ነገረ መለኮት ሲማር ብቻ ነው:: ***የእውነት መስፈርት*** (criteria for truth) የምንለው ግን፣ አበበ በተጠቀሰው ትምህርት ቤት የነገረ መለኮት ትምህርት እንደሚማር የምናውቅባቸው መንገዶች ናቸው (epistemological tests):: ለምሳሌ የዐይን ምስክሮች፣ የትምህርት ቤቱ እማኝነት:: እውነታውን የምናውቅበት መንገድ (epistemological justification) ከሰው ሰው ሊለያይ ይችላል:: አንዱ እውነታውን የሚያጣራበት መንገድ ሌላው ሰው ያንን መንገድ ላያውቀው ይችላል:: ጥንታውያኑ ሰዎች አለን በሚሉት መረጃ መሬት እንደ ሰፌድ ጠፍጣፋ ነች ሊሉ ይችላሉ:: ነገር ግን አዲስ የሆኑ መረጃዎች ከመገኘታቸው የተነሣ ቀድሞ እውነት ነው ተብሎ የሚታሰበው ነገር እውነት ሆኖ ላይገኝ ይችላል:: ከዚህ የምንማረው ቁም ነገር እውነትን የምናረጋግበት መስፈርት/መንገድ ተለየ ማለት የእውነት ቅድመ ሁኔታ ተለያየ ማለት አይደለም:: ስለዚህ፣ "መሬት ጠፍጣፋ ነች" የሚለው ጉዳይ ነባራዊ በሆነ ሁኔታ እውነት ወይም ሐሰት ነው፤ ይህ ጉዳይ ግን የእኛን የማረጋገጫ መንገድ ግምት ውስጥ ባላስገባ መልኩ ነው::

4. የአርስጣጣሊስ ሥነ አመክንዮ (Aristotelian logic) የምዕራባውያን ሥነ አመክንዮ ስለሆነ በሌላው ባህል ውስጥ እውነት መሆን አይችልም የሚል ተቃውሞ ሊቀርብ ይችላል:: ይህ አነጋገር፣ "የምዕራባውያን ሥነ አመክንዮ ከባህል ባህል የተለያየ ነው" የሚለውን ስሑት አስተሳሰብ መሠረት ያደረገ ነው:: ነገር ግን ይህ አነጋገር ራሱ እውነት ሊሆን የሚችለው ፍጹማዊ የሆነ እውነት ሲኖር ወይም የአርስጣጣሊስ ሦስቱ የሥነ አመክንዮ ሕግጋት እውነት ሲሆኑ ብቻ ነው:: እነዚህን የሥነ አመክንዮ ሕግጋት የሚጣረስ ማናቸውም ዐይነት አነጋገር እርስ በርሱ የሚቃረን አልያም ትርጉም የለሽ ንግግር ነው:: አርስጣጣሊስ እነዚህን

ሕጎች አገኛቸው ወይም አርስጣጣሊስ ምዕራባዊ ኀላፊ ነው ማለት፣ ሕጎቹም ምዕራባውያን ናቸው ማለት አይደለም።

# II. "የእውነት" ንድፈ ሐሳቦች?

ከዚህ በመቀጠል ዋና ዋና የሚባሉትን የእውነት ንድፈ ሐሳቦች በወፍ በረር እንቃኝ:—

## 1. ዝምደታዊ/ጕድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ

## (The Correspondence Theory of Truth)

ዝምደታዊ/ጕድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ምንድን ነው የሚለውን ጕዳይ በትክክል ለማብራራት የሚከተሉትን መሠረታዊ ቃላት ምን ትርጕም እንደ ወከሉ እንመልከት:—

### 1) እውነት ተሸካሚ (Truth-bearer)

እውነት ተሸካሚ የምንለው የእውነት ፋይዳው (truth value) እውነት አልያም ሐሰት የሆነውን ዐረፍተ ነገር ነው። "ሣር አረንጓዴ ቀለም ያለው ተክል ነው" የሚለው ዐረፍተ ነገር እውነት ተሸካሚ ይባላል።

### 2) እውነት ፈጣሪ (Truth-maker)

እውነት ፈጣሪ የምንለው እውነት ተሸካሚውን እውነት እንዲሆን ያደረገው ነገር ነው። "ሣር አረንጓዴ ቀለም ያለው ተክል ነው" የሚለው ዐረፍተ ነገር እውነት የሚሆነው በገሐዱ ዓለም (reality) ሣር አረንጓዴ መልክ ይዞ ሲገኝ ብቻ ነው። ሣር አረንጓዴ ቀለም ያለው ተክል መሆኑ ለቀለም አይለዬ፣ ለዐይነ ስውራን እንዲሁም ለዐይናሞች እውነት ነው። ግለሰቡ ዐይነ ስውር ሆነ ዐይናማ ወይም ግለሰቡ አረንጓዴ መሆኑን የማመኑም ሆነ ያለማመኑ የሣርን አረንጓዴ ተክልነት አይቀይረውም።

### 3) ጉድኝታዊ መስተጋብር (Correspondence relation)

ጕድኝታዊ መስተጋብር የምንለው በእውነት ተሸካሚውና በእውነታው መካከል ያለ መስተጋብር ነው። ለምሳሌ "ይበልጣል" የሚለው ቃል ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ታሳቢ ያደረገ (የግድ የሚል requires) ነው (ለምሳሌ ሰውና ሕንፃ)። ልክ እንደዚሁ ሁሉ ዝምደታዊ/ጕድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ሁለት ነገሮችን የሚያመሳክር ነው። ይኸውም ዐረፍተ ነገሩን ከእውነታው ጋር።

ጉድኝታዊ መስተጋብር (Correspondence relation)

እውነት ፈጣሪ (Truth-maker)  ↗    ↘  እውነት ተሸካሚ (Truth-bearer)

አሁን ዝምደታዊ/ጕድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ማብራራት ይቻላል። ዝምደታዊ/ጕድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ አንድ ዐረፍተ ነገር እውነት የሚሆነው፣ ዐረፍተ ነገሩ ከገሐዱ ዓለም (reality) ጋር ጥምረት/ጕድኝት ፈጥሮ (correspond) ሲገኝ ነው የሚል የእውነት ንድፈ ሐሳብ ነው። ዝምደታዊ/ ጕድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ትክክል

የማይሆነው እውነት ተሸካሚው ወይም አንድ ዐረፍተ ነገር ያለ እውነት ፈጣሪው እውነት መሆን ሲችል ብቻ ነው።

ከሚወክለው ነገር ጋር አንድ የሆነ ነገር እውነት ነው[8]። እውነት ከገሐዱ ዓለም ጋር ዝምደታዊ/ጉድኝታዊ የትስስር ባሕርይ አለው። እውነት ማለት እንደ ነገርየው የሆነ ንግግር ማለት ነው[9]። ከገሐዱ ዓለም ጋር ጉድኝት ያለው ስንል ቁሳዊ ለሆኑም ሆነ ቁሳዊ ላልሆኑ ሐሳቦች (ideas) ማለታችን ነው። ነገር ግን በሁለቱም መንገድ እውነታ (reality) ያለ ሲሆን፣ እውነት (truth) ደግሞ ከእውነታው (reality) ጋር አንድ የሆነ ወይም ጉዳዩን በትክክል የሚወክል ነው። ሐሰት ደግሞ ከእውነታው (reality) ጋር አንድ ያልሆነ ነገር አንድ ነው የሚል ነው[10]። የሒሳብ ስሌትን መሠረት ያደረጉ እውነታዎች እንዳሉ ሁሉ፣ ሐሳባዊ የሆኑ እውነታዎች አሉ። ነገር ግን በሁሉም/በሁለቱም መንገድ እውነታ ያለ ሲሆን፣ እውነት ደግሞ ከእውነታው ጋር አንድ የሆነ ነገር ነው።

አንዳንድ የዝምደታዊ/የጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ተቃዋሚዎች ኢየሱስ፣ "እኔ እውነት ነኝ" (ዮሐንስ 14÷6) ሲል፣ እውነት ሰብአዊ (personal) እንጂ ዐረፍተ ነገራዊ (Prepositional) ያለመሆኗን የሚያመለክት ነው ባዮች ናቸው። ዐረፍተ ነገራዊ (Prepositional) ያለመሆኗ ጉዳይ፣ ከገሐዱ ዓለም ጋር ጉድኝታዊ መስተጋብር የግድ እንደማያስፈልግ የሚያመለክት ነው ይላሉ። ነገር ግን ሰብአዊም ሆነ ዐረፍተ ነገራዊ እውነታዎች ከእውነታው ጋር ጉድኝት መፍጠራቸው የግድ ነው። ኢየሱስ፣ እውነት ከሆነውና የማይታየው አምላክ ጋር ፍጹም ነጸብራቅ ነው (ዕብራውያን 1÷3)። ኢየሱስ አባቱን ይመስላል (correspond) (ዮሐንስ 1÷18፤ 14÷9)።

እግዚአብሔር አብ ግን ከእርሱ ውጪ አንዳችም ነገር ስለሌለ እርሱ ራሱ እውነት ነው። እንደ ዝምደታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ እውነት የሚባለው የገሐዱን ዓለም (reality) በትክክል የሚወክል ነው ካልን፣ እግዚአብሔርን "እውነት" ነው ለማለት ከምን ጋር ተጉዳኝቶ (correspond) ነው? በሌላ አገላለጽ የእግዚአብሔርን እውነትነት (ሮሜ 3÷4) በምን ማረጋገጥ ይቻላል? የሚል ጥያቄ ሊፈጠር ይችላል። እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር የሚጐዳኝ (correspond)፣ ከቃሉ ውጪ በምንም የማይመስል አምላክ ነው። እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ለራሱ እውነት ነው። እውነት የሚለው ጉዳይ ተነጻጻሪነትን ታሳቢ የሚያደርግ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር እውነት ሳይሆን የእውነት ሁሉ መስፈርት ነው። ሌሎች ነገሮች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከእርሱ ጋር ስለሚጐዳኙ እውነት የሚባሉ ቢሆንም፣ እርሱ ግን ከእርሱ ውጪ በምንም ስለማይመስል ከአንዳችም ነገር ጋር ሊጐዳኝ/ሊዛመድ አይችልም።

ዝምደታዊ/ጉድኝታዊ የሚለው ጉዳይ ከእርሱ ውጪ ያለን ነገር ታሳቢ ያደረገ ስለሆነ፣ በዚህ መልኩ ሲታይ እግዚአብሔር እውነት ሳይሆን የእውነቶች ሁሉ መመዘኛ ነው። ከእግዚአብሔር ***ውጪ*** የሆነ ነገር ስለሌለ ንጽጽር ***ከውስጥ*** ከራሱ ጋር ብቻ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ መልኩ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ፍጹም አንድ ነው። የሚከተለውን የተሳሳተ ሙግት ይመለከቷል:—

1. ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሥልጣን የሚገዙ ሁሉ ኦርቶዶክሳውያን ናቸው።
2. ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ግን ለራሳቸው ሊገዙ አይችሉም።
3. ስለዚህ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ኦርቶዶክሳዊ አይደሉም።

---

[8] Truth is what corresponds to its referent.

[9] Truth is "telling it like it is"

[10] It tells it like it is not, misrepresenting the way things are.

ሁለተኛው የሙግት ነጥብ ስሑት ነው:: ይኸውም ርእሰ ሊቃነ ጳጳስ ለራሱ ሊገዛ ይችላል:: ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ፣ ኦርቶዶክሳውያኑ ሁሉ የሚመሩበትን ሕግ ማውጣቱ ሕጉ በእርሱ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን ሊያደርገው አይችልም:: እግዚአብሔር ለራሱ ሥልጣን የሚገዛ አምላክ ነው ስለዚህም እግዚአብሔር ለራሱ እውነት ነው::

## ይህ የእውነት ንድፈ ሐሳብ እውነት መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን?

ዝምደታዊ/ጒድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ እውነት መሆኑን እንዴት እናውቃለን የሚለውን ጒዳይ በሁለት አቅጣጫ መመለስ ይቻላል—ገላጭ/ክሥተታዊ ሙግት (Descriptive or Phenomenological argument) አንዱ ሲሆን፣ ዲያሌክቲካዊ ሙግት (Dialectical Argument) ደግሞ ሌላው ነው::

### 1. ገላጭ/ክሥተታዊ ሙግት

ዝምደታዊ/ጒድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ እውነት መሆኑን የምናሳይበት ይህ የሙግት ዘዴ አንድን ክሥተት በናሙናነት ወስዶ ከዚያ ክሥተት ስለ እውነት የተማሩትን ነገር በማሳየት ነው:: ለምሳሌ የዓለማየሁንና የዓለሚቱን ጒዳይ በናሙናነት እንመልከት:: ዓለማየሁ ከሚማርበት ትምህርት ቤት መጻሕፍት መሸጫ ሱቅ፣ እቤቱ ይደውልለትና ከውጭ አገር ተገዝቶ እንዲመጣለት ያዘዘው የፍልስፍና መጽሐፍ ተገዝቶ እንደመጣለትና መጻሕፍት መሸጫ ሱቅ ድረስ በመምጣት ያዘዘውን መጽሐፍ መውሰድ እንደሚችል ይነገረዋል:: በዚህ ጊዜ ዓለማየሁ እንዲመጣለት የሚፈልገው መጽሐፍ በመጻሕፍት መሸጫ ሱቅ ውስጥ እንዳለ አእምሮው ውስጥ ይቀረጻል::

ዓለማየሁ በአእምሮው ውስጥ የተቀረጸው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ መውሰድ የሚገባው ርምጃ ምን እንደ ሆነ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: ይኸውም ወደ መጻሕፍት መደብሩ በመሄድ መጽሐፉ መምጣቱን ማረጋገጥ እንጂ ሶደሬ ሄዶ መዋኘት አይደለም:: ወደ መጻሕፍት መሸጫ ሱቁ እየሄደ ሳለ ዓለሚቱ የምትባለው ባልንጀራው መንገድ ላይ ታገኘዋለች:: ዓለማየሁ ወዴት እንደሚሄድም ሆነ ለምን ወደዚያ ስፍራ እንደሚሄድ ለዓለሚቱ ሳይነግራት ተያይዘው ወደ መጻሕፍት መሸጫ ሱቁ ይሄዳሉ:: በመጻሕፍት መሸጫ ሱቁ ውስጥ ዓለማየሁና ዓለሚቱ የፍልስፍና መጽሐፉ፣ መጽሐፍ መደርደሪያው ላይ ተቀምጦ ያዩታል:: መጽሐፉን ማየታቸው የሁለቱም እውነተኛ ተሞክሮ ቢሆንም ለዓለማየሁ መጽሐፉ መጻሕፍት መሸጫ ሱቁ ውስጥ አለ የሚለው አስተሳሰቡ ከገሐዱ ዓለም ጋር (actual state of affiars) አንድ መሆኑን አረጋግጦአል— በዐይነ ሥጋው::

### 2. ዲያሌክቲካዊ ሙግት

ዝምደታዊ/ጒድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብን የማይቀበሉና ከዝምደታዊ/ጒድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ የተለየ "የእውነት" ንድፈ ሐሳብ ለማቅረብ የሚፈልጉ ሰዎች ንድፈ ሐሳባቸውን የሚያቀርቡት ዝምደታዊ/ጒድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ዝምደታዊ/ጒድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብን መሠረት ባደረገ መልኩ መሆኑ ንድፈ ሐሳባቸውን በተቃርኖ ውስጥ ይጥለዋል:: የሚቃወሙትን ንድፈ ሐሳብ መሠረት አድርገው ከእርሱ ጋር ተጻራሪ ንድፈ ሐሳብ መያዛቸው ንድፈ ሐሳባቸውን እውነት ነው የሚሉ ከሆነ እውነትን እየተቃወሙ ንድፈ ሐሳባችን እውነት ነው እንዴት ይላሉ:: ንድፈ ሐሳባችን እውነት አይደለም የሚሉ ከሆነ ደግሞ ሐሰትን መቀበል ያለብን እንዳችም ምክንያት የለም::

# ስለ ዝምደታዊ/ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ መታወቅ ያለባቸው ጉዳዮች

*ይህን የእውነት ንድፈ ሐሳብ በጠለለ መልኩ እንዳንረዳው ምንጩን የሚያደፈርሱብን በርካታ ስሑት ሐሳቦች ማስወገድ ያስልጋል፡፡ የተወሰኑትን እንመልከት፡—*

1. *"አንጻራዊነት እውነት ነው" የሚሉ አንጻራውያን እውነት አንጻራዊ ከሆነች፣ ይህ እውነት ሰዎች ሁሉ እንዲቀበሉት የሚገባ እውነት ሳይሆን፣ የተናጋሪው አመለካከት ብቻ ይሆናል፡፡ እውነት የሌለበትን የተናጋሪውን አመለካከት መቀበል የሚኖርብን ምክንያት የለም፡፡ "አንጻራዊነት እውነት አለ የሚለው ጉዳይ አንጻራዊ በሆነ መልኩ እውነት ነው" የሚባል ከሆነ የማዕከለ ውጋጅነትን ሕግ የሚባለውን መሠረታዊ የአመክንዮ ሕግ ስለሚጣረስ ስሕተት ነው፡፡*

2. *አንጻራዊነት ትክክል ከሆነ ዓለማችን በተቃርኖ የተሞላች ትሆናለች፡፡ ለእኔ እውነት የሆነው ነገር ለሌላው ሐሰት ከሆነ፣ ተቃራኒ ነገሮች እውነት ሊሆኑ ነው ማለት ነው፡፡* 1) *"በማቀዝቀዥው ውስጥ ሥጋ አለ"* 2) *"በማቀዝቀዥው ውስጥ ሥጋ የለም" የሚሉት ዐረፍተ ነገሮች በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ ትርጒማቸው እውነት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ እውነት መሆን ካልቻሉ ደግሞ ተቃራኒ ነገሮች እውነት መሆን አይችሉም ማለት ነው፡፡*

3. *እውነት አንጻራዊ ከሆነ፣ አንድም ሰው ሊሳሳት አይችልም፡፡ በምን መስፈርት ተሳስተሃል በምንስ መስፈርት ትክክል ነህ ይባላል?*

4. *አንጻራዊነት እውነት ከሆነ ትምህርት ሊኖር አይችልም፡፡ ትምህርት አዳዲስ መረጃዎችን ገንዘብ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የተሳሳቱ መረጃዎችንም ማስተካከል ወይም ማስወገድ ነው፡፡ አንዳችም እውነት ወይም ሐሰት ከሌለ ትምህርት ሊኖር አይችልም፡፡*

5. *በአንድ ነገር ላይ ያለን ዕውቀት ፍጹም ስላልሆነ (ነገሮችን የምናውቀው ተነጻጻሪ በሆነ መልኩ ነውና)፣ ፍጹማዊ የሆነ እውነት ሊኖር አይችልም የሚለው አስተሳሰብ ትክክል አይደለም፡፡ በርግጥ ፍጹም እርግጠኞች የሆንባቸው ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ "3+2=5" መሆኑ፤ "እኔ ሬሳ ያለመሆኔ" ("እኔ ሬሳ አይደለሁም" ስል የተናገርሁት ሬሳ ባለመሆኔ ነው)፤ ክብ-አራት ማዕዘን ያለመኖሩ ፍጹም ዕውቀት አለኝ፡፡ ነገር ግን አንጻራዊያን አንድን ጉዳይ እውነት መሆኑን የምናውቅበት ማስረጃ የለም የሚለው ጉዳይ እውነት የለም ከሚለው ጋር ያደባልቁታል፡፡ ይህ ስሕተት ነው፡፡ የምናቀርበው ማስረጃ የቱንም ያህል ጠንካራ ወይም ደካማ መሆኑ እውነታውን አይቀይረውም፡፡ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነች የሚለውን ጉዳይ ለማስረዳት አጥጋቢ ማስረጃ የለኝም ማለት እውነታው አይታወቅም ማለት አይደለም፡፡ የማስረጃ መኖርና ያለመኖር የእውነትን ፋይዳ አይቀይርም፡፡*

6. *ጥሩ መጥፎ፣ ትልቅ ትንሽ፣ እውነት ውሸት፣ ወዘተ የሚሉት ጉዳዮች ንጽጽርን ታሳቢ ያደረጉ ስለሆነ፣ ፍጹማዊ የሚባል እውነት የለም ሊባል ይችላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከሂትለር ጋር ሲነጻጸሩ ጥሩ ከእማሆይ ትሬሳ ጋር ሲነጻጸሩ ደግሞ እኩይ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይህ ጉዳይ ፍጹማዊ የሆነ እውነታ እንደሌለ የሚያሳይ ነው የሚባል ከሆነ፣ ስሕተት ነው፡፡ እኔ ከታላቅ ወንድሜ ጋር በቁመት ስንነጻጸር ከእርሱ አንሼ ብገኝም፣ ከታናሽ ወንድሜ ጋር ስነጻጸር ግብ በልጩው ልገኝ እችላለሁ፡፡ ነገር ግን ከታናሽ ወንድሜ ጋር ተነጻጽሬ መብለጤና ከታላቅ ወንድሜ ጋር ተነጻጽሬ ማነሴ ፍጹም እውነት ነው፡፡ ይህ ዐይነቱ ጉዳይ ፍጹማዊ የሆነ እውነት የለም እንድንል አያደርገንም፡፡*

7. "እውነት የማይቀያየር ቢሆን ኖሮ አዲስ እውነት አይገኝም ነበር" የሚሉ ሰዎች አሉ። "አዲስ" ስንል አዲስ የሆነው ለእኛ ነው ነገር ግን "አዲስ" የተባለው ነገር ድሮም የነበረ እውነት ነው። ሰዎች እውነትን ያገኛሉ እንጂ እውነትን አይፈጥሩም። ወርኀ የካቲት 2000 ዓ.ም ተፈጠረ/ተወለደ የሚባል እውነት የለም። ተገኘ የሚባል እንጂ። ይህም እውነት በየትኛውም ቦታና ጊዜ እንዲሁም ሁኔታ ውስጥ እውነት ነው። እውነት እንደማያረጀው ሁሉ፣ እውነት አይፈጠርም፤ አይለወጥምም። በአንድ ጊዜ እውነት የሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ እውነት ነው።

8. በአንድ ነገር ላይ ያለን ዕውቀት ጠንካራ አይደለም ማለት እውነት ፍጹማዊ አይደለችም ማለት አይደለም። ሳይንሳዊ ግኝቶች ከአሮጌው እውነት ወደ አዲሱ እውነት የሚካሄዱ ሽግግሮች ሳይሆኑ፣ ሰዎች በርእስ ጉዳዩ ላይ ያላቸው ዕውቀት እየጐለበተ መሄዱን የሚያሳዩ ናቸው። ፍጹማውያን ነን ማለት ስለ እውነት ፍጽም የሆነ ዕውቀት አለን ማለት አይደለም።

9. ፍጹማውያን ግትሮች ናቸው ይባላል—ትክክል የሆነውን ነገር ወይም አመለካከት አንቀበልም ስላልን። ነገር ግን አንጻራውያንም ቢሆኑ የእኛን ስላልተቀበሉ ግትሮች ናቸው እንላለን። ስለዚህ ወቀሳው በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚወድቅ ነው። ነገር ግን ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ ፍጹማውያን "ግትር" ሆኑት በምን ላይ ነው?—እውነትን ሙጥኝ ማለታቸው። እንዲሁም አንጻራውያን በምን ላይ ግትር ሆኑ— ውሸትን ሙጥኝ ማለታቸው። እንግዲያው ልዩነቱ እዚህ ላይ እንጂ ግትር የመሆኑ ጉዳይ ላይ አይደለም።

10. ፍጹማውያን ጠባብ ናቸው ይባላል። 4+4 መልሱ 8 እንጂ ሌሎች በቢሊዮን የሚበልጡ አማራጮች መልስ ሊሆኑት አይችሉም። ስለዚህ ስምንትን የሙጥኝ ማለት ጠባብ ነህ ሊያሰኝ አይገባውም። ይህ ጉዳይ ጠባብ የሚያሰኘኝ ከሆነ ጠባብ መሆኔ ትክክል መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እንደ እኔ ጠባብ ያለመሆናቸው ስሕተት ነው።

## 2. ቅንብራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ

(The Coherence Theory of Truth)

እንደ ቅንብራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም እምነት እውነት ነው የሚባለው አንድ ሰው እውነት ነው ብሎ ከሚያምነው ነገር ጋር ጥምረት ፈጥሮ ሲገኝ ብቻ ነው። ስለዚህ አንድን ዐረፍተ ነገር እውነት ወይም ሐሰት የሚያደርገው የገሐዱ ዓለም (reality) ሳይሆን፣ አንዱ እምነት ከሌላው እምነት ጋር ጥምረት የመፍጠሩ ጉዳይ ነው።

የዚህ ንድፈ ሐሳብ ደጋፊዎች መኻል የሚከተሉት ትልቁን ቦታ ይዘው ይገኛሉ ስፒኖዛ (1632-1677) ሔግል (1770-1831) እና ብራንድ ብላንሻርድ (1892-1987)። ቅንብራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብን ከቅንብራዊ የማስረጃ አቀራረብ ንድፈ ሐሳብ (Coherence theory of justification) መለየት ይኖርብናል። ከቅንብራዊ የማስረጃ አቀራረብ ንድፈ ሐሳብ ዝምደታዊ/ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ጋር ተዛማጅ የሆነና እውነት እውነት መሆኑን የምናጣራበትና ከዝምደታዊ/ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ጋር አንድ መሆኑን የምንለይበት መንገድ ነው።

ቅንብራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ ውስጥ የሚታየው ትልቁ ችግር ቅንብሩ የሚፈጠረው እንዴት ነው እንዲሁም አንዱ ቅንብር ከሌላው ቅንብር ጋር እንዴት እንደማይቃረን ማወቅ ይቻላል የሚለውን ጉዳይ የመመለስ ዐቅም ያማጣቱ ጉዳይ ነው።

አንድ ሰው እኔ የጥድ ተክል ነኝ እንዲሁም የጥድ ተክል ይንቀሳቀሳል ብሎ ቢያምን ግለሰቡ ይህ አስተሳሰቡ ከብዙ አስተሳሰቦች ጋር ቅንብር ቢፈጥር ግለሰቡ ትክክል እንዳልሆነ እንዴት ማሳወቅ ይቻላል? በአጠቃላይ ይህን ንድፈ ሐሳብ የተቀበለን ሰው አቋምህ ወይም እምነትህ ትክክል ነው ወይም ስሕተት ነው ብሎ ለመበየን አንዳችም ከእርሱ ውጪ ያሆነ እውነት (reality) የለም።

## 3. ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ
(Pragmatic Theory of Truth)

ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ የተዋቀረው በዊልያም ጀምስ፣ (1842-191) ጆን ድዊ (1859-1952) እንዲሁም ዘመነኞቹ ፈላስፎች በሒላሪ ፑትናም እና በሪቻርድ ሮርቲ አማካይነት ነው። እንደ ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ አንድ እውነት እውነት የሚሆነው ወይም እውነት የሚባለው ጉዳዩ ጠቃሚ ሆኖ ወይም አዋጪ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው[11]። እንደዚህ አመለካከት አንድ ነገር እውነት የሚሆነው ጉዳዩ ለሚቀበሉት ሰዎች አንዳች ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲተወቅ ብቻ ነው።

ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ አቀንቃኞች ራሳቸው አንድ ጉዳይ አዋጪ ወይም ጠቃሚ ነው በሚሉበት ትንታኔ ላይ እርስ በርሳቸው ይለያያሉ። ከዚህም የተነሣ ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ አራማጆች ራሳቸው አልቦ ዕውቀታዊ ገቢራውያንና (nonepistemic Pragmatism) ሥነ ዕውቀታው ገቢራዊነት (epistemic Pragamtism) በሚል ለሁለት ይከፈላሉ።

እንደ አልቦ ዕውቀታዊ ገቢራውያን አንድ ጉዳይ ትክክል የሚሆነው የሚፈለግ ውጤት እስካመጣ ድረስ ብቻ ነው፣ ይኸውም ደስታን የሚጨምር ሕማምን የሚቀንስ መሆኑ እንጂ በሚቀርብለት መረጃ ላይ አይደለም።

እንደ ሥነ ዕውቀታዊ ገቢራዊነት ደግሞ አንድ ነገር እውነት ነው የሚባለው (1) እውነት ለመሆኑ ምክንዩአዊ ማስረጃ ሲቀርብለት፣ (2) ማስረጃውን ምክንዩአዊ የሆኑ ሰዎች ሁሉ በቂ ወይም አጥጋቢ ማስረጃ ነው ብለው ሲቀበሉት እንዲሁም (3) ጉዳዩ የመተንተን ዐቅም ሲኖረው (explanatory Power) ነው።

ቅንብራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ እንዲሁም ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ የእውነትን ነባራዊነት የሚቃወሙ እንዲሁም አንጻራዊነትን የሚደግፉ የእውነት ንድፈ ሐሳቦች ናቸው።

[11] A belief P is true if and only if P works or is useful to have.